# ለመጭው የተቃዋሚ ድርጅቶች ስብሰባ
## ከመኢሶን የቀረበ ሰነድ
## (ረቂቅ ሃሳብ)

ሁሉን አቀፍ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብሰባ ለመጥራት በመደረግ ላይ ባለው ዝግጅት ሳቢያ ብዙ ጥናት አዘልና ጠቃሚ ትንተና የያዙ ጽሁፎች ተሰራጭተዋል። በነዚህ ጽሁፎች ላይ ሁሉ ዝርዝር ትንተናና አስተያየት መስጠት የሚያስፈልግ አይመስለንም። ሆኖም ዝርዝር ሳይገባ በተለ ይ ስላለፊው፣ ስለዛሬውና ስለመጭው ወቅትና ተግባሮቻችን አስመልክተው ከቀረቡት ሃሳቦች ላይ እየተነሳን የምንስማማባቸው ላይ ሳናተኩር ለየት ያሉና ጠቃሚ የሚመስሉንን አስተሳሰቦች በማቅ ረብ ለተሳታፊዎች ውይይት መንደርደሪያ እንዲሆኑ እንደሚከተለው ባጭር ባጭሩ እናቀርባለን።

1. ሃገራችንና ህዝባችን ወዴት እየሄዱ ነው?

«አዲስ ጎዳና ለኢትዮጵያ» በሚለውም ሆነ በሌሎቹ ጽሁፎች ሃገራችን ዛሬ ስለምትገኝበ ት አሳሳቢና «አሳፋሪ» ሁኔታ በሰፊው ተዘርዝሩዋል። መጠነ ሰፊ ርሃብ፤ ልክ የሌለው ድህነት፤ ኤይድስ ወዘተ እየተባለ፣ በማስረጃነትም ብዙ ጠቃሚ አሃዞች እየቀረቡ የህዝባችን ሰቆቃ በግል ጽ ተቀምጧል። እነዚህ ሁሉ በዚህ መልክ ተዘርዝረው በመቅረባች ጽሁፉን ያቀረቡት ወገኖች ያ ደረጉትን ሰፊ ጥረት የሚያሳይና የሚያስመሰግናቸው ነው። ነገር ግን የቀረቡት አሃዞች ምን ያህል አስደንጋጭ ቢሆኑም በኛ ግምት ሃገራችንና ህዝባችን የሚገኙበትን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ሙሉ በ ሙሉ ለመረዳት አሁን ካለንበት ሁኔታ ዘልቀን ሌላ መሰረታዊ ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል።

«ሃገራችንና ህዝባችን ወዴት እየሄዱ ነው?» አጭሩ መልሳችን ኢትዮጵያችንን እንደሃገር ህዝባችንን እንደ ሰብአዊ ፍጡር ህልውናቸውን በመፈታተን ላይ ያሉት ቀውሶችና ችግሮች ከአ መት አመት መመለሻ በሚያስቸግርበት ሁኔታ እየተባባሱ በመሄድ ላይ ናቸው የሚል ነው። ይህን ን ለመረዳት ሁለት ነጥቦችን አስመልክተን ስጋታችንን እንግለጽ። አንደኛው ነጥብ ርሃብና መና ጢ ድህነትን ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የኤችአይቪ ኤይድስን መቅሰፍት ይመለከታል።

ህዝባችን ከእለት እለት የባሰ ድህነት ውስጥ እየዘቀጠ ይገኛል። በአለፊው አመት ይፋ ሆ ኖ የነበረ የአለም ባንክ አሃዝ ከሃያ አመት በፊት 190 ዶላር ይገመት የነበረው የሃገራችን የነፍስ ወከፍ ገቢ ወደ 108 ዶላር ወርዷል ይል ነበር። ከሁለት ወር በፊት የወጣ ሌላ ስታቲስቲክስ እን ደሚያሳየው ደግሞ በያዝነው አመት ይህ ገቢ አሽቆልቁሎ 89 ዶላር ደርሷል። ከስምንት ወራት በፊት «ሴቭ ዘ ችልድረን» በተባለ በጎ ሰናይ ድርጅት የቀረበ ጥናት ይህንን የማዝቀጥ ሂደት በ ተጨባጭ አሳይቷል። ጥናቱ ሁለት አመታት ይህል የፈጀና በወሎ ገጠሮች አራት ሚልዮን ህዝ ብን ያካተተ ጥናት ቢሆንም አቅራቢዎቹ እንዳሉት ይህ ግኝት ለመላ ሃገሪቱ ሊሰራ የሚችልና የ ተያያዘችውን አስደንጋጭ የጥፋት ጎዳና የሚያመለክት ነው።

አጥኝው ቡድን በተባለው አካባቢ ያሉትን ዜጎች ከሶስት ይከፍላቸዋል።

የመጀመሪያዎቹ የከፉ ማጣት ያጠቃቸው ወይም «ዴስቲቱት» የሚላቸው ሲሆኑ የአካባቢ ው ህዝብ *«ውሃ አንፉሪ»* ብሎ የሚጠራቸው ናቸው። ለምግብም ሆነ ለሌላ ለማንኛውም ለኑሮ አስፈላጊ ለሆነ ነገር ከውጭም ከዛው ከአካባቢውም በሚያገኙት ምጽዋት ብቻ የሚኖሩ ናቸው። የዛሬ አስር አመት ከህዝቡ 5.5% ብቻ ነበሩ። ዛሬ ቁጥራቸው ጨምሮ ከጠቅላላው ህዝብ 14.6 % ሆነዋል። መሰረታዊ የሆነ የአቅጣጫ ለውጥ ካልተደረገ በቀር በአስር አመት ውስጥ ከህዝቡ ከ21% በላይ ይሆናሉ። ከኢትዮጵያ ህዝብ ከአንድ አምስተኛው በላይ ምጽዋተኛ ይሆናል ማለት ነው።

ሁለተኛዎቹ *«ከውሃ አንፉሪዎች»* ሻል ያሉና ጥናቱ *«በቋፍ የሚኖሩ»* ወይም «ቭልነረብል » ብሎ የሚጠራቸው ዜጎች ናቸው። ድርቅ ወይም ሌላ ከባድ ቀውስ ካልመጣ በስተቀር ከእጅ ወደአፍ ለሆነ ኑሮ በቂ አላቸው። ትንሽ ቀውስ ሲመጣ ምንም መጠባበቂያ ስለሌላቸው ወዲያው ኑ ወደ *«ውሃ አንፉሪነት»* ይወርዱና ማንሰራራት አቅቷቸው ብዙውን ጊዜ በዚያው ቀልጠው ይቀ

ራሉ። እነዚህ ዜጎች የዛሬ አስር አመት ከህዝቡ 17.4% ነበሩ። ዛሬ ከህዝቡ ግማሽ በላይ ወይም 54.9% ሆነዋል።

ሶስተኛው ራሳቸውን ችለው የሚኖሩና በአንድ አመት የተከሰተ ቀውስ ተደጋግሞ እስካል መጣ ድረስ ኑሮዋቸውን የማያናጋባቸው አልፈው ተርፈውም አንዳንዴ ለአካባቢያቸውም ሲተርፉ የሚችሉ ጥናቱ ራሱ በቅንፍ «ሃብታሞች» ብሎ ያስቀመጣቸው ዜጎች ናቸው። የዛሬ አስር አመ ት ከህዝቡ 77% ነበሩ። ዛሬ ወደ 30% ወርደዋል።

በኤች አይቪ ኤይድስ ጉዳይም «ቀጣዩ ማእበል» ወይም «ዘ ኔክስት ዌቭ» በሚል በሲአ ይኤ የቀረበው ጥናት እንደዚሁ መጭውን ጊዜ አስደንጋጭ የሚያደርግ ነው። የተጠቆሙት አም ስት አገሮች ቻይና፣ ረሽያ፣ ህንድ፣ ናይጀሪያና ኢትዮጵያ ናቸው። የኤይድስ መቅሰፍት በነዚህ በአጠቃላይ ከአለም ህዝብ 40% በሚያካትቱት አገሮች ገና «መንደርደሪያ ደረጃ» ወይም «ኢኒ ሻል ፌዝ» ላይ ነው ካለ በኋላ ዛሬ በጠቅላላው ወደ ሃያ ሶስት ሚልዮን የሚገመተው በሽተኛ በ ሰባት አመት ውስጥ ሰባ አምስት ሚልዮን እንደሚደርስ ይጠቁማል። በጥናቱ መሰረት ከነዚህ አ ገሮች ከሁሉም ይበልጥ የሚጠቁት ኢትዮጵያና ናይጀሪያ ናቸው። በኛ አገር ይህ ቁጥር አሁን ካ ለበት 2.7 ሚልዮን በሰባት አመት ውስጥ ወደ አስር ሚልዮን ከፍ እንደሚል ይናገራል። በፐርሰን ቴጅ ደረጃ ከሄድን ደግሞ በሰባት አመታት ውስጥ በበሽታው የሚለከፈው ህዝብ ወደ 18% ከፍ እንደሚል ጠቁሙዋል። ከህዝባችን አንድ አምስተኛው ግድም የኤይድስ ሰለባ ይሆናል ማለት ነ ው።

በመጭው ጊዜ ዛሬ ሃገራችንን ወጥረው የያዟት ችግሮች እየከፉና እየሰፉ የሚሄዱት በርሃ ብና በኤይድስ ብቻ አይደለም። ከነሱ ተያይዞ የአካባቢ ውድመት አለ። ድህነት የሚያባብሰው ይኸ የአካባቢ ውድመት ችግር በራሱ ደግሞ የድህነት መንስኤ እየሆነ በመሄዱ ሃገራችን አስከ ፊ አዙሪት ውስጥ እንደምትገኝ ግልጽ ይመስለናል። ተዲያ በነዚህ አጣዳፊ ችግሮች አንጻር ምን እናድርግ?

ይህንን አሳሳቢና ከእለት እለት እየተበላሸ የሚሄድ አጣዳፊ ችግር በበጎ ራእይና ጊዜ የሚ ጠይቁ ስትራቴጂያዊ አላማዎችን በማስቀመጥ ብቻ ልንወጣው አንችልም። አዲስ ጎዳን የሚለው ጽሁፍ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ «ለኢትዮጵያ ተሃድሶ» ይሟገታል። ሃገራችን ምንም ያህል የከፋ ች ግር ቢደቀንባት በአኩሪ ታሪኳ፤ በስብጥርጥርና አሸብራቂ የህዝቿ ባህል፤ በነዚህ ህዝቦቿ ታታሪነ ትና አስተዋይነት፤ በታደለችው ይህ ነው የማይባል የተፈጥሮ ሃብት፣ ጥራ ግራ ባፈራቻቸው ም ሁራን ልጆቿ ብርታት በሃያ አምስት አመታት ውስጥ አንድ «ኢትዮጵያዊ ተአምር» ማከናወን እ ንደምትችል በሚገባ ተቀምጧል። በዚህ ሙሉ በሙሉ እንስማማለን። ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ አስከፊና አስቸጋሪ በመሆኑ ችግሮቻችንን ከዚህ አስቸጋሪና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ብቻ ተነስተን ለመያያዝ ከሞከርን የትም እንደርስም የሚል ጽኑ እምነት አለን። ራእይ ያስፈልገናል። ከተጨባ ጩ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ለዚች አገራችንና ለዚህ ህዝባችን ከአለንም ህልም መነሳት ይኖርብናል ። ይህ ራእይና ህልም እንደዚህም ደግሞ ለዚህ እውንነት አስፈላጊ የሆኑት የአስተሳሰብና የፖሊ ውስ ለውጦችና ተሃድሶዎች በጽሁፉ በተደረገው መልክ በበርካታ ገጾች በዝርዝር መቀመጣቸው ተገቢ ነው። አንዳንድ ቦታ የሚደጋገሙት ነጥቦች ተስተካክለውና አንዳንድ ቦታ አነስተኛ ማሻሻ ሎች ተደርገውባቸው ተተርጉመው በሰፊው መሰራጨት ይገባቸዋል።

እኛም ይህንን ራእይ ጨብጠን በሱም እየተመራን ለአጣዳፊ ችግሮቻችን አጣዳፊና ተጨ ባጭ መልሶችን መሻት ይኖርብናል። ይህንን ለመንደፍ ደግሞ ዛሬ ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ መቀ ጠል የማትችልበት ደረጃ ደርሳለች ከሚለው አስደንጋጭ ድምዳሜ መነሳት ይኖርብናል። በዚህ ከቀጠለች በአጭር ጊዜ ውስጥ መመለሻ የሌለው የጥፋት ደረጃ ትደርሳለች ከሚለው እምነት ተነስተን ዛሬ ይህንን የጥፋት ሂደትና አዙሪት አንድ የሆነ ቦታ ለመስበር ምን ተጨባጭ ነገር እ ናድርግ የሚለው ጥያቄ የስብሰባው ዋና የውይይት ነጥብ መሆን ይገባዋል። ለዚህም ባለፈው በጋ ራ ያደረግነው ጥረት ለምን የታሰበውን ፍሬ አልሰጠም የሚለውን ጥያቄ አቅርበን መመለስና ከሱ ትምህርት ቀስመን ባለፈው ጥረት ላይ እየገነባን ወደፊት እንድንራመድ የሚያስችለን ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርብናል።

## 2. ያለፈው ራእይና ያለፈው ጥረት ምን ደረሰ? ለምን አልሰራም?

ላለፉት አስር አመታት ተቃዋሚዎች አጥፊውን የወያኔ መንግስት በህዝብ ትግል አስወግደ
ው ለሃገራችንንና ለህዝባችን የተሻለ ቀን ለማምጣት በጋራ እንዋደቃለን ብለው በተነሱ ቁጥር ደ
ግመው ደጋግመው ያስቀመጡዋቸው የጋራ አላማዎች አሉ። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሃገር
አንድነት፣ በዚች አንድነቷና ሉአላዊነቷ በተከበረባት አገር ሉአላዊ የሆነ ህዝብ፣ በዚህ ህዝብ ፊ
ት ተጠያቂ የሆነ ከዴሞክራሲያዊ ምርጫ የፈለቀ መንግስት.....እየተባሉ ራእዮቻችን በሚገባ ተቀ
ምጠዋል። ነጻ ምርጫ ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ፤ የሃገር አንድነት ሲሉ ምን ማለታቸው እ
ንደሆነ፣ ዴሞክራሲያዊ ህገመንግስት ሲሉ ይህ ሰነድ እንዴት መረቀቅ እንዳለበትና ዴሞክራሲን፣
የሃገር አንድነትንና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ምን ምን መሰረታዊ ይዘቶች ሊኖሩት እንደሚገ
ባ በተደጋጋሚ በተለያዩ <u>የጋራ</u> ሰነዶች እየተዘረዘሩ ተቀምጠዋል።

ከእነዚህ «የራእይ ሰነዶች» መሃከል ለምሳሌ ከፓሪስ አንድ የፈለቀው የስምንት የብሄርና
ህብረብሄር ድርጅቶች ተወካዮች የተሳተፉበት «የብሄራዊ እርቅና ሰላም ኮንፈራንስ አስተባባሪ ኮ
ሚቴ» ከስምንት ወራት በላይ ተወያይቶበት ለአዲስ አበባው የግዮን ጉባኤ ያቀረበው «የመንደር
ደሪያ ሰነድ» አለ። ከዚያም አማራጭ ሃይሎች ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ ያጸደቀው «ለአዲስ
ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ» የተሰኘው ሰነድ፣ ከዚያም በፓሪስ ሁለት ጉባኤ የጸደቀው «የዴሞክራሲ
ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም» የሚለው ሰነድ አለ። እነዚህን ሰነዶች የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃቸ
ዋል። በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን በተለያዩ መንግስታትና በአውሮፓ ፓርላሜንት «ለኢትዮጵያ
ሁለ ገብ ቀውስ መፍትሄ» ተብለው በውሳኔ ድጋፍ ያገኙ ናቸው።

እስካሁን ግን ነጻ ምርጫ ብለን በሃገራችን ነጻ ምርጫ አልተካሄደም። ዴሞክራሲያዊ ህገ
መንግስት ብለን ብንነሳም የአንድ አናሳ ድርጅት የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፕሮግራም የሃ
ገሪቱ የበላይ ህግ ተብሎ የተደነገገበት ሁኔታ ውስጥ ነን። ላለንበት ችግር መፍትሄው እስከዚህም
በዚህ የተቃዋሚዎች ስብሰባ ከሚሳተፉት ድርጅቶች አብዛኞቹ ፓሪስ፣ ለንደን፣ አዲስ አበባና እ
ንደገና ፓሪስ ተሰብስበው ባጸደቁዋቸው የጋራ ሰነዶቻ ከተንጸባረቀው የጋራ ራእይ ይበልጥ አርቆ
የሚያይና ይበልጥ የሰፋ ሌላ ራእይ ማቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም። እነዚህን ተቀብሎ የእስካ
ሁኑ ጥረት ለምን አልሰራም በሚለው ጥያቄ ሰፊ ውይይት ያስፈልጋል። ከጉድለቶች አስፈላጊው
ን ትምህርት ቀስሞ ሁሉን ነገር በአዲስ ለመጀመር ሳይሆን ባለፈው ጥረት ላይ ለመገንባት የሚያ
ስችለን አዲስ የትግል ስትራቴጂ ማውጣት ይኖርብናል።

ያለፈውን የትግል ተመክሮ በሚመለከት አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቡዋል። በዚህ ጽሁፍ
ውስጥ ያለፈው ጥረት ለምን ፍሬ እንዳልሰጠ ብዙ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። በአብዛኞቹ እንስ
ማማለን። ግን ደግሞ የምናካሂደው የፖለቲካ ትግል እንደመሆኑ መጠን ለትግላችን ፍሬ አልባነት
ከአስር በላይ ምክንያቶች ሲደረደሩ በዚህ ጥናት ላይ የችግራችን <u>ፖለቲካዊ ምክንያት</u> አልተነሳ
ም። በኛ ግምት ግን ዋናው ምክንያት ይኸ ነው። መፍትሄ ተብለው በተዘረዘሩት በተቃዋሚ ሃይ
ሎች መሃከል ይበልጥ መተማመን መፍጠር፣ የጠራ የስራ ክፍፍል ማድረግ፣አንዱ ከሌላው አብ
ጦ ለመገኘት የሚያደርገውን ጥረት ማቆም ወዘተ እየተባሉ የተዘረዘሩት ጉድለቶች እርግጥ መታ
ረም ያለባቸው ናቸው። ነገር ግን የድክመታችንን የፖለቲካ ምክንያቶች ካልተረዳንና እነሱን ለማ
ረም አስፈላጊ የሆኑትን የትግል ዘዴ ለውጦች ካላደረግን ትግላችን አንዲት ስንዝር ወደፊት አይ
ራመድም። ትኩረት ያስፈልጋቸዋል የምንላቸውን የፍሬ አልባነታችንን <u>የፖለቲካ ምክንያቶች</u> ምን
ም እንኳን የተያያዙ ቢሆኑም ከሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል።

### <u>*ሀ) ራእያችንና ሰነዶቻችን ብቻቸውን በወያኔ ላይ የማያወሳዳ የፖለቲካ የበላይነት አሳስ ጨበጡንም።*</u>

ዴሞክራሲ አልን ነጻ ምርጫ፣ ሰብአዊ መብቶች አልን የህግ የበላይነት፣ መድበለ ፓርቲ
ስርአት አልን የሃገራችን አንድነት የነዚህ ጥሪዎች ችግራቸው ወያኔ እኔም አምንባቸዋለሁ ማለቱ
ብቻ አይደለም። ከተቃዋሚዎች ይልቅ እኔ በተግባር እያዋልኳቸው ነው ባይም ነው። ዝም ብለ
ን ለዴሞክራሲ መስፈን፣ ለሃገር አንድነት ወዘተ ማለትን ትተን «ለእውነተኛ» ዴሞክራሲ መስፈ

ን፣ «ለሃቀኛ» የሃገር አንድነት ወዘተ እያልን ማስተካከያ ቅጽል ብንለጥፍባቸው እንኳን ወያኔ እውነተኛው የኔ ነው፤ ሃቀኛው የኔ ነው እያለ ማወናበዱንና መመጻደቁን አያቆምም።

እኛ ግን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ቅጥፈት መሆኑን አውቀን እርግጥም ለሃቀኛ ዴሞክራሲ፤ እርግጥም ለእውነተኛ የህዝቦች አንድነት፤ በእውነት ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሻለ ቀን እንታገላለን። ትልቁና ልብ ያላልነው (ወይም መቀበል ያልቻልነው) ሃቅ ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በዚህ ትግል በመፋለም ላይ ያለነው ሁለት አናሳ ሃይሎች ነን። በአንድ በኩል ወያኔና ካድሬዎቹ። በሌላ በኩል ተደራጅቶ ለመታገል የሚሞክረው የነቃ አገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ሃይል። በዚህ ትግል እነዚህ ሁለት አናሳ ሃይሎች ያሏቸው የትግል ምርኩዞች የተለያዩ ናቸው።

አናሳው ወያኔ የመንግስት የፋይናንስ አቅም አለው። የመንግስት የመረጃ መረብ፤ የፖሊስና የጦር ሰራዊት አለው። በዚህ ተመርኩዞ በሃገር ደረጃ ያንሰራራና በህዝብ ላይ የተጫነ የካድሬዎች መዋቅርና ሰራዊት አለው። ከህዝቡ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆነውን ገበሬ በመሬት ስሪቱ አስሮ ይዞታል። ዲፕሎማሲያዊ ምርኩዝ አለው።

አናሳዎቹ እኛ ከነዚህ ውስጥ ማንኛቸውም የሉንም። ይህንን ድክመታችንን ካልተወጣንና ከወያኔዎች ይበልጥ ጠንክረን ካልተገኘን፣ በህብረተሰባችን ውስጥ ዛሬ በማያወላዳ ሁኔታ ለአፋኙ መንግስት የሚያደላውን የሃይል ሚዛን ካልቀየርን እንኳን የሚቀጥለውን ቀርቶ እስከ ወዲያኛው ድረስም ቢሆን ምርጫ ተሳትፈን አሸንፈን በሃገራችን ዴሞክራሲን አናሰፍንም።

እኛ አናሳዎቹ በአናሳው ኢህአዴግ ላይ የበላይነት የማግኘታችን ተስፋ አንድና አንድ ብቻ ነው። ይኸውም በሚያራምደው ፖለቲካ ምክንያት ወያኔ ፈጽሞ ሊደርስበት የማይችለውን በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን ማሰለፍ ብቻ ነው። ዛሬ ያለን የሞራል የበላይነት፤ ዛሬ ያለን የሃገር ፍቅርና የዴሞክራሲያዊነት የበላይነት በጸረ ህዝቡና በጸረ ዴሞክራሲው ወያኔ ላይ ተጨባጭ የፖለቲካ ትርጉም የሚኖረው በዚህ መልክ ህዝባችንን ከጎናችን አሰልፈን ስንፋለመው ብቻ ነው። መራራ ሃቁን እንቀበል ካልን ዛሬ ይህንን የሞራልና የሃገር ፍቅር የበላይነት በፖለቲካ የበላይነት መመንዘር እንዳልቻልን ግልጽ ነው። ይህ ቢኖረን እስካሁን ድል ተቀዳጅተን ነበርና። እንደሚታየው ከሆነ ይህን የፖለቲካ የበላይነት ለመጎናጸፍ የሚደረገው ጥረት የራሱ ችግር አለው።

## *ለ) በስትራቴጂያዊ አላማዎችና በራእይ ብቻ ህዝብን ማንቀሳቀስ አይቻልም።*

ያለፉት አስራ አንድ አመታት የትግል ጉዞ ያሳየን አንድ ነገር በአነገብናቸው ክቡር ስትራቴጂያዊ መፈክሮች አማካኝነት ብቻ ህዝባችንን በሚልዮን እየቆጠርን አንቀሳቅሰን በሃገሪቱ ያለውን የሃይል ሚዛን መቀየር አለመቻላችንን ነው። እርግጥ ነጻ ምርጫ በተባለው የወያኔ ግርግር ተገቢ ተሳትፎ አድርገናል። ውጤቱ ምን እንደሆን ከወዲሁ እየታወቀ ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ አጋጣሚውን በመጠቀም ተዋድቀናል። በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በርግጥም የኢትዮጵያ ህዝብ በሚልዮን እየተቆጠረ ታሪካዊና አኩሪ ተሳትፎ አድርጉዋል። ግን የምርጫ ትግል በየአምስት አመቱ በሚከሰት ተሳትፎ የሚወሰን ትግል ነው። እንዳየነው ከሆነ ያ የብዙዎቻችንን ተስፋ ቀስቅሶ የነበረ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ዛሬ ከስሟል። አሁን ደግሞ ለሚቀጥለው ምርጫ ለዛሬ ሁለት አመት እየተዘጋጀን ነው። ህዝባችንን እንደገና በሚልዮን እየተቆጠረ እንዲንቀሳቀስ እናደርጋለን። በምርጫው ያለጥርጥር «እንሸነፋለን»። አምኖን ተነስ ስንለው ከተነሳው ታጋይ ህዝባችን የተወሰነውን ወያኔ ካድሬዎች አይንና ጥርስ ውስጥ እንዲገባ አድርገን ደግሞ በተሸናፊነት ለምንወጣበት ለ2003 ዓ.ም. ቀጣይ ምርጫ እንዘጋጅ እንላለን።

በመሃል ምድር ቢናወጥ፤ ሰማይ ቢደረመስ ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ እምርታ የምንቀሰቅስበትና ይህንን ህያው አድርገን የምንቀጥልበት «መፈክር»ም ሆነ አላማ አምጡ ሲባል ግራ እንጋባለን። ህዝብ በሚልዮን ተራብ ብለን ሰልፍ አንወጣም፣ ሰራተኛው በአንጉል ሙሰኛና አድላዊ «የነጻ ገበያ» ተብየ ኢኮኖሚ ጉረሮው ተዘጋ ብለን ሰልፍ አንወጣም፤ ሃገራችንን የባእዳን ሸቀጥ ማራገፊያ ያደረጋት አሰራር ነጋዴውንና የሃገሪቱን አምራች ለኪሳራ ሲዳርግና የስርቶ አደሩን ጉረሮ ሲዘጋ አይተን እንዳላየን እናልፋለን፤ ድህነት እየከፋ ሲመጣ፣ ስራ አጥነት እየተስፋፋ ሲኬድ፤ ካለፉት ስርአታት የወረስናቸውን ማህበራዊ ችግሮች ሳንወጣ በነሱ ላይ አዳዲስ ማህበራዊ ችግሮ

ች ሲደራረቡብን፤ አገራችን በአለም የሚታዩ ቀውሶች ሁሉ ቋት ሆና የዋይታና የሰቆቃ አገር ስ
ትሆን ለነዚህ ችግሮች የምናቀርበው አማራጭ መፍትሄ የለንም። ባጭሩ ከአስር አመታት ወዲህ
እየተባባሱና እየከፉ ለመጡት ችግሮች ገፈት ቀማሽ ለሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ በደፈናው ዴሞ
ክራሲ፤ የህግ የበላይነት፤ ነጻ ምርጫ ከሚሉት ነገሮች አልፈን ለገበሬው ወገናችን «ለርሃብና ላስ
ከፊ ድህነት የዳረገህ የወያኔ ፖሊሲ ይኽ ነው፣ እኛ ደግሞ ይህንን አማራጭ ፖሊሲ እናራምዳለ
ን» ለሰራተኛው «የችግርህ መንስኤ ይህ የወያኔ ፖሊሲ ነው እኛ ደግሞ ይህንን እናቀርብልሃለን
»፣ ለነጋዴው፣ ለአሰሪው፣ ለአምራቹ እንደዚሁ «የኛ ይኽ ነው የወያኔ ይኽ ነው» በሚል የምና
ቀርበው ምንም አማራጭ የለንም። ይህ ወደ ሶስተኛው የድክመቶቻችን ምክንያት ያመጣናል።

***ሐ) የእስካሁኑ ትግል ለህዝብ ችግር «ታገስ ዴሞክራሲ ሲሰፍን እናያለን» በሚል የመፍት
ሄ ቀን ቀጠሮ የሚሰጥ ትግል ነው።***

ተቃዋሚ ሃይሎች ህብረት ለመፍጠር በሞከሩባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ በስትራቴጂያዊ አ
ላማዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚያደርጋቸው አንድ መሰረታዊ አስተሳሰብ አለ። ለትግላችን
መንደርደሪያ የምናደርገው አስተሳሰብ፤

«ዛሬ በሃገራችን ያሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች የየራሳቸው የሆነ ርእዮተ አለም፣ የፖለቲካ፣
የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፕሮግራም አንግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ናቸው። እንደዚህም በመ
ሆኑ ሃገራችንንና ህዝባችንን ወጥረው ለያዙዋቸው ሶስዮ ኢኮኖሚክ ችግሮች አንድ የጋራ አማራ
ጭ ማቅረብ አይችሉምም አይጠበቅባቸውምም። ዛሬ የሚያስፈልገው ልዩነቶቻቸውን አቻችለው
የጋራ በሆኑት የዴሞክራሲ፣ የነጻ ምርጫ፣ የህግ የበላይነት ወዘተ ጥያቄዎች ላይ በጋራ መታገል
ነው።በነዚህ ጥያቄዎች ላይ በጋራ ታግለው ድል ሲያደርጉና በሃገራችን ዴሞክራሲ ሲሰፍን ያኔ
ሁሉምየተለየ ፕሮግራሙን አንግቦ ለህዝብ ምርጫ ይቀርባል። የኢትዮጵያ ህዝብ ከነዚህ የተለያዩ
አቋሞች ያሻውን ይመርጥና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይቋቋማል። ያኔ ተጨባጭ ችግሮቹን መፍ
ታት እንጀምራለን።» የሚል አስተሳሰብ ነው። በአጭሩ ያለን ፍልስፍና «እንዴት እንሸጋገር?» ከ
ሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ይልቅ «በባሻገሩ» ላይ ያተኮረ ፍልስፍና ነው።

ይህ አጉል ፍልስፍናችን የህብረት ትግሉን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ድርጅት በነጠላ የሚ
ያካሂደውን ትግል እንዳኮላሸው ዛሬ ለሁላችንም ግልጽ መሆን አለበት። የህብረቱ ትግል «ለሁሉ
ም የጋራ በሆኑ መፈክሮች» ላይ አተኩራለሁ ሲል ምንም ክቡር ቢሆኑ ለእለት ተእለት የህዝብ
ትግል በማይመቹ ስትራቴጂያዊ መፈክሮች ተንሳፎ እንዲቀር ተገዷል። ይህ «የጋራው ትግል በጋ
ራ መፈክር ላይ ያተኩር» የሚለው አካሄድ ልክ ይሆን የነበረው የህብረቱ አባላት የሆኑት «የተለ
ያየ ፕሮግራም» ያላቸው ድርጅቶች ሁሉም በየበኩላቸው ያላቸውን የመፍትሄ አማራጭ አነንግበ
ው ለዚህ ፕሮግራማቸው «ይመቻል» ወይም «ሪሴፐቲቭ» ይሆናል የሚሉትን «ኮንስቲቲወንሲ»
የማንቀሳቀስ ትግል ቢያካሂዱ ብቻ ነበር። ይህ «ኮንስቲቲዎንሲ» የመገንባት ትግል ምናልባት «
በብሄሮች መብት» እና «በኢትዮጵያ አንድነት» ጥያቄዎች ላይ ይታይ ይሆናል። በሃገራችንን ሶ
ስዮ ኢኮኖሚክ ጥያቄዎች ላይ ግን የሚታየው አዝማሚያ በአመዛኙ «ለጊዜው ሙያ በልብ» የ
ሚል ፍልስፍና ሆኖ ይታያል። በህብረቱ ብቻ ሳይሆን በነጠላ ድርጅቶችም አካባቢ *«አሁን ዴሞ
ክራሲ በሌለበት ሁኔታ እነዚህን ወገናዊ የሆኑ መፍትሄዎች ማቅረብ አላስፈላጊና ትርፍ ድካም ነ
ው። መጀመሪያ ዴሞክራሲ «እንዲሰፍን» በጋራ እንታገል አማራጫችንን «ከድል ባሻገር» ለህዝ
ብ እናቀርባለን»* የሚል አስተሳሰብ አለ።

ያለንበት አጥፊ አዙሪት እንግዲህ ግልጽ ነው። ዛሬ ህዝባችንን ወጥረው ከያዙት የህልው
ና ችግሮች አንጻር «ቂሱም ዝም መጽሃፋም ዝም» የተባለው ሁኔታ ውስጥ ነን። መፍትሄዎቹ ዴ
ሞክራሲ ሲሰፍን ተብሎ ቀነ ቀጠሮ ተይዞላቸዋል። እንግዲህ ችግሩ ግልጽ ነው። ዴሞክራሲ እን
ዲሰፍን የሚደረገው ትግል ግቡ የሚደርሰው ተቃዋሚ ሃይሎች በትጥቅ፣ በገንዘብ፣ በድርጅት አ
ቅምና በዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ከነሱ ልቆ ከሚገኘው ወያኔ ይልቅ የተሻለና ተጨባጭ አማራጭ
ይዘው ህዝባችንን በደርዘን ሚልዮን እያስቆጠሩ ከጎናቸው ሲያሰልፉ ብቻ ነው። ይህንን አማራ
ጭ ካላቀረቡ ህዝቡን ማንቀሳቀስ ስለማይችሉ መጀመሪያውኑ ዴሞክራሲ የሚሰፍንበት ሁኔታ የለ

ም። አማራጭ ለማቅረብ ደግሞ ዴሞክራሲን የሚጠብቁ ከሆነ እኛም ሃገራችንም አስከፊ የጥፋት አዙሪት ወይም «ቪሸስ ሰርክል» ውስጥ መሆናችን ግልጽ ይመስለናል።

በነዚህና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ተቃዋሚ ሃይሎች ተጨባጭ ሶስዮ ኢኮኖሚክ አማራጮች አቅርበው ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ የሃይል ሚዛን ባልፈጠሩበት ሁኔታ ነጻ ምርጫ፣ የህግ የበላይነት፤ ዴሞክራሲ እያሉ ያካሄዱት ትግል ላለፉት አመታት አልሰራም። በዚህ አይነት አካሄድ በመጭዎቹም አመታት ሃገራችንን ከጥፋት አድነን የሰላም፤ የብልጽግና፤ የህዝቦች ወንድማማችነት ምድር እናደርጋታለን ብሎ ማሰብ አደገኛ ህልም ይመስለናል።

3. እንዴት እንቀጥል? በአለፈው ላይ እንዴት እንገንባ?

ከጉባኤው መንደርደሪያ ሰነድ ለመረዳት እስከቻልን ድረስ ስለ ቀጣዩ ሂደት ያለው ሮድ ማፕ ዋና ዋና ነጥቦች ሶስት ናቸው። ከዚህ ጉባኤ አንድ ኮሚቴ ይፈልቃል። ይህ «የሰላም፣ የእርቅና የሃገር ግንባታ ብሄራዊ ኮሚቴ» አላማው በኮንፌራንሱ የተዘረዘሩትን አላማዎች በተግባር ለመተርጎም አስፈላጊ የሆኑትን ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ ሲሆን በተለይ ደግሞ ስብሰባው በሚያጸድቀው መንታ (ደብል ትራክ) ስትራቴጂ ላይ አተኩሮ እንዲሰራ ይጠበቅበታል።

የዚህ ስትራቴጂ አንደኛ ገጽታ መጭውን ምርጫ የሚመለከት ነው።

ተቃዋሚ ሃይሎች ሁኔታዎች ከፈቀዱ፣ አለም አቀፍ ታዛቢዎች ከተገኙና የወያኔ መንግስት በዚህ ኮንፌራንስ ከተሳተፉት ድርጅቶች አንዱንም የማግለል እርምጃ ካልወሰደ በዚህ ምርጫ መሳተፍ ይቻላል። ነገር ግን ወያኔ ይህንን ሰላማዊ ውድድር ከተቃወመና ከኮንፌራንሱ ተሳታፊ ድርጅቶች አንዱን እንኳን ቢያገልል ሁሉም ተሳታፊ ድርጅቶች ምርጫውን ቦይኮት አርገው ወደ ቀጣዩ አማራጭ የሚሄዱበትን ሌላ ጉባኤ ይጠራሉ።

በዚህ በሁለተኛው አማራጭ መሰረት ኮሚቴው አንድ ሁሉን አቀፍ የመላ ኢትዮጵያ ጉባኤ ይጠራል። በዚህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ የኢህአዴግ መንግስት ተወካዮች፤ የሲቪኩ ማህበረሰብ ተወካዮች፤ እውቅ ኢትዮጵያውያን፤ የሙያ ማህበራት፤ የትምህርት የፕሬስ ተወካዮች ይጋበዛሉ። ከአለም አቀፉም ህብረተሰብ የተባበሩት መንግስታት፤ የአፍሪካና የአውሮፓ ህብረት እንዲሁም እውቅ አለም አቀፍ ድርጅቶች በታዛቢነት ይገኛሉ። ጉባኤው «የሰላም፣ የብሄራዊ እርቅና ግንባታ የሽግግር መንግስት» የሚቋቋምበትን ዘዴ መክሮ ተግባራዊ በማድረግ በኢህአዴግ ቁጥጥር ስራ ያለውን የአሁኑን መንግስት ይተካል።»

ከፍ ብለን ከጠቀስናቸውና ትግላችንን አጨናግፈዋል ካልናቸው የፖለቲካ ጉድለቶች ስንነሳ ይህ አይነቱ አካሄድ ከሚያቀርባቸው መልሶች ይልቅ የሚቀሰቅሳቸው ጥያቄዎች በርካታ ሆነው እናገኛቸዋለን። መጀመሪያ ስለምርጫው ጉዳይ እናንሳ። ከዚያ ደግሞ ስለ ሽግግሩ መንግስት ጉዳይ ያለንን አስተሳሰብ እንሰነዝራለን።

በምርጫው ጥያቄ ሶስት ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል። አንደኛ ለመሳተፍም ሆነ ቦይኮት ለማድረግ የሚቀርቡት መስፈርቶች ጉዳይ። ሁለተኛ ምርጫ የተባለው ሂደት በጠቅላላው ለሰላምና ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ልንሰጠው ስለሚገባው ሚና ሶስተኛ ደግሞ የምርጫው ሂደት በትግላችን አወንታዊ ሚና እንዲኖረው እንዴት እንዘጋጅበት?

*ሀ) የመስፈርቶች ጉዳይ።*

ለመሳተፍ ወይም ላለመሳተፍ የመስፈርቶች መሟላት ጉዳይ ከተነሳ አይቀር በአማራጭ ሃይሎችም ሆነ በፓሪስ ሁለት አንድ ምርጫ ነጻ እንዲባል፤ አንድ ምርጫ ፍትሃዊ እንዲባል፤ አንድ ምርጫ ሃቀኛ እንዲባል እየተባለ በዝርዝር የቀረቡ አለም አቀፍ መስፈርቶች እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ መስፈርቶች ገና ሰፊ ቅስቀሳ ባይደረግባቸውም በነጻ ጋዜጦችም ሆነ በተለያዩ ሰነዶች ለኢትዮጵያ ህዝብ ቀርበዋል። በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ለምሳሌ የአውሮፓ ፓርላሜንት ወያኔ በነዚህ አለም አቀፋዊ መስፈርቶች መሰረት ምርጫ እንዲያካሂድ ጥሪ የሚያደርግ ውሳኔ አሳልፉዋል። ለመጭው ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ መሆን እነዚህ እንዲከበሩ እንታገላለን ብሎ በግልጽ ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው እንላለን።

እነዚህ መስፈርቶች ሳይሟሉ በሚደረገው ምርጫ ባለፉት ምርጫዎች «እንታዘባለን» ብለ
ው መጥተው የኛን ትዝብት አትርፈው የተመለሱት አለም አቀፍ ታዛቢዎች ካልተገኙ አንሳተፍ
ም የሚለው ቅድመ ሁኔታ ብቻውን ምን ትርጉም አለው? እነዚህ መስፈርቶች ሳይሟሉ አምስት
ም ሆነ አምስት ሽ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የመሳተፋቸው ጉዳይ ምን የሚለውጠው ነገር አለ? ዞሮ
ዞሮ ደግሞ አንድ ምርጫ ነጻ እንዲባል በሃገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ፓርቲ ቀርቶ ግለሰብ እንኳ
ን በምርጫ የመሳተፍ የማይገሰስ መብት አለው ተብሎ በግልጽ መቀመጡ እየታወቀ «ከዚህ ምር
ጫ ማንም ሆነ ማንም መገለል የለበትም» የሚል አቋም መያዝ ሲያስፈልግ እንዴት ተብሎ «ወ
ያኔ ከዚህ ኮንፈራንስ ተሳታፊ ድርጅቶች አንዱን እንኳን ከምርጫው ካገለለ ሁሉም ፓርቲዎች
ምርጫውን ቦይኮት ያደርጋሉ» ይባላል?

በዚህ ጉዳይ ማለት የምንፈልገው ሁለት ነገሮች ነው።

መጀመሪያ ለኢህአዴግም፤ ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ግልጽ ማድ
ረግ ያለብን ትግላችን ዛሬ በመላው አለም የጸኑትና በጋራ ሰነዶቻችን የሰፈሩት የነጻ ምርጫ መስ
ፈርቶች የተሟሉበት ምርጫ እንዲካሄድ የሚደረግ ትግል ነው።

ሁለተኛ በመጨረሻ ደቂቃ ውሳኔ ምርጫውን «ቦይኮት» ለማድረግ ያለን መብት እንደተ
ጠበቀ ሆኖ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ባይሟሉ እንኳን የምርጫውን «ካምፔይን» «ቦይኮት» አናደ
ርግም። በዚህ «ካምፔይን» ባለ በሌለ ሃይላችን ተንቀሳቅሰን ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ የቆረጥን
መሆኑ ከወዲሁ በግልጽና በይፋ መቀመጥ ይኖርበታል። ይህንን ስናደርግ ደግሞ ምን ጠብቀን እ
ንደሆንና ምን ስትራቴጂ ነድፈን እንደሆነ ለኛም ሆነ ለሚመለከተው ሁሉ ከወዲሁ ግልጽ ማድረ
ግ ይኖርብናል።

*ለ) ከወያኔ ምርጫ ከሂደቱ እንጂ ከውጤቱ ምንም አንጠብቅም።*

ማንም ቢሆን ከነዚህ ምርጫዎች ተቃዋሚ ሃይሎች ድል አድርገው ይወጣሉ የሚል ህል
ም የለውም። በመጭው ምርጫ ኢህአዴግ እንደተለመደው «አሸናፊ» ሆኜ ወጣሁ እንደሚል እ
ኛም፣ ወኔም፤ የኢትዮጵያ ህዝብም አለም አቀፍ ኮሙኒቲም ያውቁታል። ምናልባት ብዙ ሰው ያ
ላጤነው ሌላም አሳሳቢ ጉዳይ አለ። በየትም ይኬድ በየት ከምርጫው ውጤት ለሃገራችን ምንም
በጎ ነገር አይወጣም። ወያኔ ቢያሸንፍ የሃገራችን ሁኔታ ከመሻሻል ይልቅ እየተበላሸ የመሄዱ አ
ደጋ ግልጽ ነው። ነገር ግን ደግሞ ተቃዋሚዎች በሆነ ተአምር በአሸናፊነት ቢወጡ እንኳን «አ
ሁንስ ይችን አገር በቃሽ አላት» የምንልበት ደረጃ ላይ ደረሰን ማለት አይደለም። ችግራችን አ
ይፈታም። ለምን?

ኢትዮጵያ ዛሬ የምትተዳደረው እንደማንኛውም ስታሊናዊ ህገመንግስት የአንድ አናሳ ድር
ጅት የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፕሮግራም የሃገሪቱ «የበላይ ህግ» ተብሎ በተደነገገበት «
ፕሮግራማዊ ህገመንግስት» ስርአት ነው። ከሆነ ምርጫ አንድ ድርጅት የተለየ አማራጭ ሶስዮ
ኢኮኖሚክ ፕሮግራም ይዞ በአሸናፊነት ቢወጣም ይህንን ፕሮግራሙን በተግባር ለመተርጎም «ህገ
መንግስቱ» አይፈቅድለትም። 51% አግኝቶ መንግስት አቋቁማለሁ የሚለው ሃይል የተመረጠበትን
ፕሮግራም ለመተግበር በቅድሚያ «ህገ መንግስቱን» መቀየር ይገደዳል። ለምሳሌ መሬት መሸጥ
መለወጥ ብሎ የተመረጠ መንግስት ቢሆን ይህንን ለመተግበር ህገ መንግስቱን ለማሻሻል መጀመሪ
ያ በመአከላዊ ደረጃ በሁለቱም ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ ድጋፍ ድምጽ ያስፈልገዋል። ከዚያ
ደግሞ በሁሉም ክልሎች ምክር ቤቶች አብላጭ ድምጽ ማግኘት አለበት.......

ይህንን እያወቅን ስለምርጫ ተሳትፎ የምናወራው ከውጤቱ ምንም ነገር ጠብቀን እንዳልሆ
ነ ግልጽ ነው። «ካምፔይኑ» ውስጥ የምንሳተፈው ካወቅንበት ሂደቱ ላይ በማተኮር ለዚች አገርና
ለዚህ ሰማእት ህዝብ ቀን እንዲወጣላቸው በምናደርገው ተጋድሎ የማይናቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ
እንችላለን ከሚል ጽኑ እምነት ተነስተን ነው። ይህ ሂደት ምን ይመስላል የሚለውን ጥየቄ ከመ
መለስ በፊት መጀመሪያ ምን መሆን እንደሌለበት ያለንን አስተሳሰብ እንስጥ።

ትግላችን የምርጫ ሰሞን ግርግር ሳይሆን እንደ ዴሞክራሲ፤ እንደ የህግ የበላይነት፤ እ
ንደ አገር አንድነትና ዴሞክራሲያዊ ህገመንግስት የመሳሰሉ ዘላቂ አላማዎችን ከገበሬው፣ ከሰራቶ

አደሩ፤ ከነጋዴው፣ ከአሰሪው የእለት ከእለት የህልውና ችግሮችና ትግል ጋር አጣምሮ በወያኔ አ ገዛዝ ላይ የሚነሳ ህዝባዊ ማእበል የመቀስቀስና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ እንዲቀጥል የማድረግ ትግ ል ነው። በምርጫ ሰሞን አይወሰንም። አንድ ምርጫ «ከተጠናቀቀ» በኋላ «የዛሬ አምስት አመ ት ደግሞ በተመሳሳይ ፕሮግራም እስክንገናኝ...» ብለን ከህዝባችን አንሰናበትም። ትግላችን ከዚያ በፊት ይጀምራል። በምርጫው ሰሞን ያይላል። ይህ ማእበል እንዳለፈው ልምዳችን በምርጫው ማግስት እንዳይከስም ከወዲሁ ጥንቃቄና ስትራቴጂ አውጥቶ መጓዝ የኛ ፋንታ ነው።

ይህንን ሂደት ህያው እናድርግ ካልን አንዳንድ ከወዲሁ ወደ ጎን መተው ያለባቸው አካሄ ዶች አሉ። ያለንበት የምርጫና «ህገ መንግስታዊ» ስርአት በአንድ ፓርቲ ህገመንግስት ስር «የ መድበለ ፓርቲ ምርጫ» እየተባለ የሚሾፍበት አስገራሚ ስርአት ነው። ከፍ ብለን እንዳልነው አ ንድ ተቃዋሚ ፓርቲ የተለየና ወገናዊ የሆነ አማራጩን ይዞ ቢወዳደር መጀመሪያውኑ አያሸንፍም እንጂ ቢያሸንፍስ በዚህ ሁኔታ የት ይደርሳል? የትም አይደርስም። በመሆኑም አሁን ባለንበት የት ግል ደረጃ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች ወገናዊ የሆኑ አማራጮቻቸውን ይዘው ከህዝብ ፊት መቅረባቸው የጋራውን ሂደት ከመከፋፈልና ከማዳከም በቀር በ«ውጤት» ደረጃ ም ንም የሚያስገኝላቸው ነገር አይኖርም። ይህንን ካልን ዘንዳ በዚህ በምርጫ ጉዳይ ልናነሳ ወደ ም ንፈልገው ወደ ሶስተኛው ነጥብ እንምጣ።

### *ሐ) በህዝባችን ፊት «እኛና እነሱ» ብለን በጋራ መንቀሳቀስ ይኖርብናል።*

በዚህ ምርጫ ሳቢያ ህዝባዊ ማእበል መቀስቀስና ይህ ማእበል ደግሞ እንዳለፈው ጊዜ በ ምርጫው ማግስት ከመክስም ይልቅ እየተቀጣጠለ እንዲቀጥል ከፈለግን በቀጣዩ ምርጫ ተቃዋሚ ሃይሎች በህዝብ ፊት በአንድነት መቅረብ ይኖርብናል። ይህ ማለት እያንዳንዱ ድርጅት የቆመለ ትን የርእዮተ አለም፤ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፕሮግራም ርግፍ አርጎ ይተው ማለት አ ይደለም። እንደያዘ ይቆያል። ነገር ግን ደግሞ ካለፉት አመታት ድክመቶቻችን ትምህርት ቀስመ ናል ካልን «የጋራ» የሚባለው ትግል ስትራቴጂክ በሆኑ መፈክሮች ብቻ ከቀጠለ መንሳፈፋችንም ይቀጥላል ማለት ስለሆነ ወደ ህዝባችን «ለመውረድ» ለዚህ ህዝብ አጣዳፊ የህልውና ችግሮች አማራጭ የጋራ ፕሮግራም ነድፎ መታገሉ አስፈላጊነት ዛሬ ከመቸውም ይበልጥ ግልጽ ይመስለና ል። ስለሆነም ዛሬ ዋና ተግባራችን ይህ ህዝባችን በተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ከተለያዩና ከተ ሰበጣጠሩ አማራጮች ይሆነኛል የሚለውን የሚመርጥበት «የቅንጦት» ሁኔታ አስኪደርስ ድረስና እንዲያውም እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ዛሬ «መርጦም ምንም ለውጥ ለማያመጣበት ምርጫ» አማ ራጮች መንጋጋታቸው ምንም ፋይዳ አይኖረውም። የወያኔ ፕሮግራም አለ። የኛ አነስተኛ አማራ ጭ ፕሮግራም መኖር አለበት። <u>*ጊዜያዊ የሆነ ግንባር ፈጥረን ምርጫውን በኛና በነሱ መሃል*</u> ማድ ረግ ለትግሉ ጥራት፤ጥንካሬና ዘላቂነት የማይናቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ይህ ጊዜያዊ የሆነ አነስተኛ የጋራ ፕሮግራም የማውጣቱ ጉዳይ አንገብጋቢ የሚሆነው በም ርጫው ለመሳተፍ ብቻ አይደለም። ከፍ ብለን በጠቀስነው ለኮንፈራንሱ የቀረበው የመንደርደሪያ ጽሁፍ ላይ መጭውን ምርጫ «ቦይኮት» ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ቦይኮት ከተደረገ ወዲያውኑ አ ንድ አገር አቀፍ ጉባኤ ተጠርቶ የኢህአዴግን መንግስት የሚተካ ሌላ «የሰላም፤ የእርቅና የመልሶ ግንባታ ብሄራዊ መንግስት» እንዲቋቋም ይደረጋል የሚል አማራጭ ስትራቴጂ ተሰንዝሯል።

እንዲህ አይነቱ የሽግግር መንግስት አስፈላጊና የሚቻል ሲሆን ምን አይነት ተግባርና ምን አይነት ስልጣን ሊኖረው እንደሚገባ፣ ዞሮ ዞሮ ደግሞ በዚህ የሽግግር ወቅት ምርጫ የማዘጋጀቱን ና፣ በጠቅላላው በሃገሪቱ የሚካሄደውንና የሚያስፈልገውን የሰረጸ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የማስፈኑ ጉዳይ ለማንም «የሽግግር መንግስት» መተው እንደማይገባና ከዚህ ይልቅ እንደ ደቡብ አፍሪካ አይነት አንድ «የዴሞክራታይዜሽን ኮሚሽን» መቋቋሙን እንደምንመርጥ ይህ ምርጫችን ደግሞ ለምን እንደሆነ « ተሸጋጋሪው ማነው? አሸጋጋሪውስ?» ብለን ባቀረብነው ጥናታዊ ሰነድ አስተሳሰ ባችንን ሰንዝረናል።

የሆነ ሆኖ በተለይ የወያኔ መንግስት በሆነ ሁኔታና አጋጣሚ ቢፍረከረክና አገሪቱ ከባድ ቀ ውስ ውስጥ ብትገባ ይህን መንግስት ተክቶ የሚሰራ አንድ መንግስት አስፈላጊ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ለኮንፈራንሱ የቀረበው የመንደርደሪያ ሰነድ የዚህ የመንግስት መቋቋም አማራጭ የሚቀርበ

ው ወያኔ ባቀረብነው መስፈርት መሰረት ምርጫ አላዘጋጅም ካለና የብሄራዊ ውይይትን ሃሳብ አ ሻፈረኝ ማለቱን ከቀጠለ እንደሆነ ይናገራል። ነገር ግን ወያኔ ብሄራዊ ውይይትንና ነጻ ምርጫን በፊቱ አሻፈረኝ የሚለው እነዚህን ጥያቄዎች እንዲቀበል የግድ አስፈላጊ የሆነውን የህዝብ ጫ ና መቀስቀስና ይህንን መንግስት ወጥረን ለመያዝ አቅም ስላነሰን እንደሆነ ግልጽ ነው። ታዲያ እ ንዴት ተብሎ ነው በአቅመ ቢስነታችን ጣፊያ ጠይቀን ሲነፈገን ከዚያው አቅመቢስነት ሳንወጣ ታናሽና ታላቅ የምንጠይቀው? ውይይት አሻፈረኝ ካልክ እንዴት ነው ስልጣን የምታካፍልበት አገ ር አቀፍ ጉባኤ ላይ ተገኝና የሚተካህ መንግስት ይቋቋም የሚባለው? ወያኔስ ቢሆን ምን ገዶትና ምን አስገድዶት ነው እንዲህ አይነቱ ጨዋታ ውስጥ የሚገባው?

ይህ አባባላችን የሽግግር መንግስት ሃሳብን የመቃወም አቋም አያንጸባርቅም። ለዚህ አስፈ ላጊ የሆነውን የፖለቲካ ሃይል ሚዛን የማመቻቸቱ ተግባር ላይ አተኩረን እንስራ ማለት ብቻ ነ ው። እንዲያውም ትግላችንና በዚህ ትግል በወያኔ ሰፈር የምንቀሰቅሰው ቀውስ አንድ የተወሰነ ደ ረጃ ሲደርሱ ይህ ጥያቄ አፍጥጦና አግጦ የሃገር ሰላምና ህልውናን ጥያቄ ሊሆን በሚችል መል ኩ ሊቀርብ ይችላል። በዚህም የተነሳ አንድ ተተኪ መንግስት ማቋቋም አንገብጋቢ የሚሆንበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ከፍ ብለን ያቀረብነው «አነስተኛ የጋራ ፕሮግራም» ይነደፍ የሚለው ሃ ሳብ የቀረበበት አንዱም በዚህ ምክንያት ነው።

ይህ አነስተኛ ፕሮግራም ካሁኑ ይነደፍ ስንል ነገ ሃገራችን ከፍተኛና ካሁኑ የባሰ ቀውስ ውስጥ ስትገባና ህልውናዋ፣ ደህንነቱዋና ጸጥታዋ አደጋ ላይ ወድቀው የዚህ አይነት መንግስት አ ስፈላጊነት አፍጥጦና አግጦ ሲመጣ «ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ» እንዳንባል ብቻ አይደለም። ዛሬ ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው ሰሞንና ከምርጫውም ባሻገር ህዝብን ቀጣይነት ባለው ሁኔ ታ በጋራ ለመቀስቀስና ከባድ ቀውስ ቢመጣ ደግሞ ይህ ቀውስ ለወያኔ እንጂ ለሃገራችን እንዳይ ተርፍ ከፈለግን እንዲህ አይነቱ ህዝብ በጋራ የመቀስቀሻና ለሽግግሩ ዘመን የሃገር መስተዳደር መ መሪያ የሚሆን ጊዜያዊ የጋራ ፕሮግራም የግድ ያስፈልገናል።

## 4. ለአዲስ እምርታ ባለ 3 ነጥብ ፕሮፖዛል

ዛሬ ሃገራችንና ህዝባችን በታሪካቸው አይተው የማያውቁት ቀውስና ችግር ላይ ናቸው። ከዚህ ለመውጣት ሃገርና ህዝብ ለመምራት ሃላፊነት አለብን ብለን በትግል ላይ የምንገኝ ሃይሎ ች መክረንና ዘክረን ለዚህ ሁኔታ ተመጣጣኝ የሆነ የትግል ስትራቴጂ አውጥተን መንዝ ይኖርብና ል። «የምንነድፈው ስትራቴጂ ከዚህ በፊት በየትም ያልታየ ነው፣ ውስብስብ ነውና አይሰራም፤ ህዝባችንን ላያንቀሳቅስ ይችላል ወዘተ» እያልን መፍራትና ማመንታት የለብንም። የተለያዩ ህዝቦ ች የተለያዩ «ኦሪጂናል» ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ለነጻነት ተጋድሎዋቸው ፖለቲካዊና ስነልቡናዊ እምርታዎች (ዳይናሚክሶች) ሲቀሰቅሱና ድል ሲያደርጉ ተመልክተናል። የቤኒን ህዝብ «ብሄራዊ ና ባለሙሉ ስልጣን ኮንፈራንስ» ብሎ በሰላማዊ ትግል የኬሪኩን መንግስት ገልብጦዋል። ማዳጋ ስካር ለስድስት ወር ያልተቋረጡ ሰላማዊ ሰልፎች አይተናል። በቀድሞይቱዋ ምስራቅ ጀርመን የ ሰኞ ሰኞ ሰልፎች ለለውጡ ትግል ያደረጉትን አስተዋጽኦ እናውቃለን ወዘተ...

በኛ አገር እስካሁን «ከተለመዱት» የትግል ስልቶች ወጣ ተብሎ የሞከርነው ነገር እምብ ዛም የለም። ወያኔ ህዝብ ይጨፈጭፋል። ተቃውመን መግለጫ እናወጣለን። ወያኔ ምርጫ አዘጋ ጀሁ ይለናል ወይ «ቦይኮት» እንላለን ወይ ደግሞ ምንም የማንጠብቅበት ግርግር ውስጥ ዘው ብለ ን እንገባለን። ዛሬ ማሰብ ያለብን ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታና ከዚህ ድክመታችን ተነስተን ምን አይ ነት ድፍረትንና የፈጠራ ችሎታን የሚያንጸባርቅ ስትራቴጂ አውጥተን እንንቀሳቀስና «መመለሻ የ ሌለው» ህዝባዊ የትግል ማእበል እናንቀሳቅስ በሚለው ጥያቄ ላይ ነው። በኛ በኩል በመንደርደ ሪያው ሰነድ የቀረቡት በተለይ አንድ «የኢኮኖሚና ማህበራዊ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ» እቅድ የሚነድፍ የኢትዮጵያውያን ኤክስፐርቶች ቡድን ስለማቋቋም፤ ለመጭው ትግላችን የኢትዮጵያ ውያንን የፋይናንስና የማቴርያል አቅም ለማሰባሰብ መደረግ ስላለበት የተቀነባበረ ጥረት በሚጠቁ ሙት ሃሳቦች ሙሉ በሙሉ እንስማማለን። ከዚህ በተጨማሪ ከፍ ብለን ከሰነዘርናቸው ሃሳቦችና ትንተናዎች- አንጻር ትኩረት ቢሰጣቸው ይጠቅማል ከሚል እምነት በመነሳት ለጉባኤው ሶስት ሃ ሳቦች እናቀርባለን።

1ኛ/ ጊዜያዊ የጋራ የሽግግር አማራጭ ፕሮግራም መንደፍ

ይህ ጊዜያዊ የሽግግር አማራጭ የጋራ ፕሮግራም የህዝባችንን ህልውና በሚነኩ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጥያቄዎች ላይ ወያኔ እንደ መንግስትነቱ ከቀየሳቸውና ከስራ ላይ ከሚያ ውላቸው አጥፊ ፖሊሲዎች አንጻር እኛ ደግሞ እንደተቃዋሚነታችን የምናቀርበውን የጋራ አማራ ጭ መፍትሄ የሚያካትት ሰነድ ይሆናል። የሽግግሩን ዘመን ለማብሰር በሚደረገው ትግል ህዝባች ንን የምንቀሰቅስበት የጋራ መሳሪያ ነው። የትግሉ ማእበል እንዲያይልና በዚህ ትግል በወያኔ ላይ በሚደርሰው ቀውስ አንድ የሽግግር መንግስት የሚቻልና አስፈላጊም ሲሆን ይህ መንግስት ከስራ ላይ የሚያውለው ይህንን ፕሮግራም ይሆናል። ሰነዱ በጣም ዝቅተኛና የተለያዩ ፕሮግራሞች ካላ ቸው ድርጅቶች ሰነዶች የሚውጣጣ የ«ኮምፕሮማይዝ» ሰነድ ስለሆነ ይዘቱ እስከዚህም የሃገሪቱ ን እድል ለሃያ ለሰላሳ አመት በሚወስኑ ከባድ የፖሊሲ ምርጫዎች ላይ የሚያተኩር አይሆንም። ከሽግግሩ ባሻገር ህዝቡ ሁኔታዎች ተመቻችተውለት ያሰኘውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ አወቃቀር እስኪመርጥ ድረስ ይህ የጋራ ፕሮግራም በርሃብ፣ በኤይድስ፤ በኢንዱስትሪ፤ በንግድ፤ በአካባቢ ብክለትና እንክብካቤ በመሳሰሉት ጥያቄዎች አሁን ሃገራችንና ህዝባችን የተያያዙትን የማዝቀጥ ሂደት መግታት እንደ ዋና አላማው አርጎ የሚወስድ ሰነድ ይሆናል።

2ኛ ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ

ከፍ ብለን ባልነው መሰረት በዚህ የትግል ምእራፍ ጎልቶ መውጣት የአለበት የትግላችን « እኛና እነሱ» የሚለው ገጽታ በመሆኑ በመጭው ምርጫም እያንዳንዱ ድርጅት የራሱን ወገናዊ አማራጭ ፕሮግራም ይዞ ህዝብ ፊት መቅረቡ እንኳን ሽንፈት ተደግሶለት ቀርቶ ከምርጫ በአሸ ናፊነት ቢወጣም ከትግሉ ሂደት አንጻር ምንም ፋይዳ አይኖረውም። ከዚህ ይልቅ ሁሉም ድርጅ ቶች በጋራ የተነደፈውን የሽግግር ፕሮግራም አንግበው በህዝብ ፊት ቢቀርቡ ይመረጣል። ይህ ማለት በየምርጫ ጣቢያው ከተቃዋሚው ወገን ከአንድ በላይ ተወዳዳሪ አይቀርብም ማለት ነው። ይህ አካሄድ ራሱን የቻለ ጠቀሜታ አለው። ባለፈው ምርጫ እንደታየው ከሆነ 550 የሚጠጉ የ ምርጫ ጣቢያዎች ሲኖሩ ተቃዋሚዎች በወከባም ሆነ በሰው ሃይል ማጣት ሁሉንም መሸፈን አል ቻሉም ነበር። ከሁለት መቶ በላይ በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎችን የኢህአዴግ «ተወዳዳሪዎች» የ ተወዳደሩት ከራሳቸውና አንዳንዴም ከግለሰቦች ጋር ብቻ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ጣቢያዎች ከተቃዋሚዎች ወገን ሁለትም ሶስትም ተደራርበው ሲወዳደሩ ታይተዋል። አሁን በሚ ቀርበው ሃሳብ መሰረት «በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የተቃዋሚዎች ተወካይ» በሚል አሰራር ከሄድን አገሪቱን የማላበሱ እድላችን እንደሚጨምር ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ ለሌላው ለምናቀር በው ሃሳብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

3ኛ. አንድ «ተተኪ ሸንጎ» ስለማቋቋም

ከምርጫው ውጤት ሳንጠብቅ ሂደቱ ላይ እናተኩር ማለት ይህንን የምርጫ እንቅስቃሴ የ ጋራ ፕሮግራማችን በህዝባችን ውስጥ ስርጾ ቅባሎት የሚያገኝበትን፣ ይህ በምርጫው ሳቢያ የሚ ቀሰቀሰው ህዝባዊ የትግል ማእበልና ወኔ የማይከስምበትን፤ ቀጣይነት እንዲኖረው ትግላችን በተሻ ለ የሚዋቀርበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት እንጠቀምበት ማለት ነው። ሂደቱ ላይ እናተኩር ማለት ወያኔ ከዳር እስከዳር ተቆጣጥሮና አጭበርብሮ ከምርጫው በአሸናፊነት ወጣሁ ቢልም ይህንን ውጤት ከመጤፍ አንቆጥረውም ማለት ነው። «በህግ» እንጂ በፖለቲካ ወያኔ አላሸነፈንም ማለ ት ነው። «በህግ» እንጂ በፖለቲካ ይህ ውጤት ተቀባይነት የለውም ማለት ነው።

በተጭበረበሩ ምርጫዎች ማግስት «ተሸናፊ» የተባሉት ተቃዋሚዎች የተደረገውን ማጭበ ርበር አጋልጠው ይኸንን ውጤት አንቀበለውም ብለው መግለጫ ማውጣታቸው በተለያዩ የአለም ክፍሎች በተደጋጋሚ የታየ ክስተት ነው። በኛም አገር ባለፈው ምርጫ ማግስት ተቃዋሚ ድርጅ ቶች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ይህንን የተጭበረበረ ውጤት እንደማይቀበሉት አውጀዋል። ነገር

ግን ምርጫውን ከፊቱ ጥቂት ወራት ከኋላው ደግሞ ጥቂት ሳምንታት ብቻ እንደሚያስቆጥር « ዝግ ምእራፍ» እንጂ በረጅሙ የትግል ስትራቴጂያችን እንደ ክፍት ሂደትና እንደ አንድ ግጥሚ ያ ባለመወሰዱ በዚህ ተቃውሞ ላይ የተገነባ ምንም ነገር ሊኖር አልቻለም። ነገሩ እንዳለቀለት ነ ገር ተቆጥሮ ወደ ሌላ ነገር፤ ወደ ሌላ ትግል ታለፈ። በመሃል ያ ሚሊዮኖችን ያንቀሳቀሰ ትግል ተበትኖና ፊዞ ጊዜው ሲደርስ ደግሞለሌላ ምርጫ ዝግጅት እየተጀመረ ነው።

ይህ ስህተት እንዳይደገም ከፈለግን ያለን አንድ አማራጭ ነው። ከዚህ ምርጫም በፊት ሆነ በምርጫው እንቅስቃሴ የሚነሳሱትን ሚሊዮኖች እንዳለፈው ጊዜ በትተናቸው ወደ ሌላ ነገር እንደማናልፍ ለኢትዮጵያ ህዝብም፤ ለኢህአዴግም፤ ለአለም አቀፉም ኮሙኒቲ ከወዲሁ ግልጽ ማድረግ ይኖርብናል። «በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የተቃዋሚዎች ተወዳዳሪ» በሚለው መመ ሪያ የምርጫ ጣቢያዎችን በሙሉ ሸፍነን፣ ህዝባችንን በያለበት በአንድ የጋራ ፕሮግራም ዙሪያ ከ ካንቀሳቀስን እነዚህ ተወዳዳሪዎቻችን በወያኔ የምርጫ ቦርድ «ተሸንፋችኋል። አልቆላችኋል» ስ ለተባሉ ብቻ አያልቅላቸውም። በየጣቢያቸው ሃያም፣ ሰላሳም፣ አርባም ከመቶ ብቻ አግኝታችሁ «ተሸንፋችኋል» ቢባሉም ሌላው ቀርቶ የወያኔ ምርጫ ቦርድ ራሱ በሰጠው በዚሁ «የእምነት ቃ ል» መሰረት በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የሚወክሉ ህዝባዊ ሃይሎች ናቸው። አንበትናቸውም። በምርጫው ማግስት ከመላ ሃገሪቱ ተጠራርተው ከወያኔ «የተወካዮች ምክር ቤት» አንጻር ወይም ፓራሌል የሆነ አንድ የራሳቸው «ተተኪ ሸንጎ» እንዲያቋቁሙ ሃሳብ እናቀርባለን።

በዚህ ሃሳብ ስምምነት ካለ ስለዚህ «ተተኪ ሸንጎ» አላማ፤ አወቃቀር፤ አሰራር፤ በውጭ የሚገኙ ድርጅቶች ተሳትፎ ጉዳይንና ሌሎች ዝርዝር ነጥቦችን ከዚህ ጉባኤ ለሚፈልቀው አስተባ ባሪ ኮሚቴ ወይም ለዚሁ ጉዳይ ኮንፈራንሱ ለሚሰይመው «አድሆክ» ኮሚቴ ዝርዝር ሃሳብ ለማ ቅረብ ዝግጁ ነን።

ከወዲሁ ማለት የሚቻለው ግን ይህ ያለንበትን የጥፋት አዙሪት ለመስበር ያስችላል የምን ለው «ደፋርና ኦሪጂናል» ሃሳብ ቅባሎት ካገኘ የእነዚህ አምስት መቶም ይሁን ከዚያ በላይ የሚ ሆኑ ምልምሎቻችን አካሄድ ከወዲሁ ሶስት ስብሰባዎችን ያካትታል

መጀመሪያ ከምርጫው በፊት የምዝገባው ስነስርአት እንደተጠናቀቀ አዲስ አበባ ተሰብስበ ው ከህዝብ ፊት ይዘው ስለሚቀርቡት የጋራ ፕሮግራም፣በዚህ ምርጫ እንቅስቃሴ ስለሚከተሉት የጋራ ስትራቴጂ፣ የወያኔን አሻጥሮች ስለሚቋቋሙበት ዘዴ፤ ስለትግሉ አጠቃላይ ቅንብር በሚነደ ፍ ስትራቴጂ ላይ ተወያይተው ስምምነት ይደርሳሉ። በየመንደሩና በየምርጫው ጣቢያ የሚካሄደ ው ትግል የየመንደሩና የየምርጫው ጣቢያ ትግል ብቻ ሳይሆን በውጭ ሃገር የሚኖሩ በሚልዮን የሚቆጠሩና ከዳር እስከዳር የኢትዮጵያ ህዝብ በጋራ የሚያካሂደው ትግል እንደሆነ የጨበጡትን ግንዛቤ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያበስራሉ። «ካምፔይኑን» በዚህ መንፈስ ያካሂዳሉ።

ሁለተኛው በምርጫው ዋዜማ የሚጠራ ሌላ ስብሰባ ይሆናል። የዚህ አላማ ተወዳዳሪዎቻ ችን በየአካባቢያቸው ስላካሄዱት ትግል፤ ስላጋጠማቸው ችግር፣ በወያኔ ካድሬዎች ስለተፈጸሙት ህገወጥ ድርጊቶች፣ ምርጫ ቦርዱ ስላሳየው አድልኦ ወዘተ ሰፊ ግምገማ ማካሄድና ዝርዝር ሪፖ ርት ማቅረብ። ከዚህ ግምገማ በኋላ ተሳታፊዎቹ «ከካምፔይኑ» ዘልቀው ምርጫው ውስጥ ይሳተ ፉ እንደሆን ወይም ደግሞ ሁሉም በአንድነት «ቦይኮት» ያደርጉ እንደሆን እስከ ምርጫው ዋዜ ማ በእንጥልጥል እንዲቆይ መደረግ ባለበት ጥያቄ ላይ አቋም ይወስዳሉ። ይህንን የጋራ ውሳኔያ ቸውን ከነምክንያታቸው ዘርዝረው ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲ የሚያስረዱበት መግለጫ ያወጣሉ። እንደዚሁም ስለ «ተተኪው ሸንጎ» በሚቀርብ ሰነድ ላይ ዘርዘር ያለ ውይይ ት አካሂደው ይህ ሃሳብ ደግሞ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነትና ድጋፍ እንዲያገኝ ስለሚያደርጉት ቅስ ቀሳ ይዘት ስትራቴጂ ያወጣሉ።

ሶስተኛው ስብሰባ በምርጫው ማግስት የሚደረግ ሲሆን ከተወሰነ ጊዜ ውይይትና በዚህ ጉ ዳይ ሁሉም በየአካባቢያቸው ህዝባችን ግንዛቤ እንዲያገኝ ቅስቀሳ ካደረጉ በኋላ የሲቪኩ ማህበረ ሰብ፣ የምሁራን፤ የታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተወካዮችና የአለም አቀፍ ኮሙኒቲ ታዛቢዎች የሚገኙበት የ«ተተኪ ሸንጎው» መስራች ጉባኤ ስብሰባ ይሆናል።

እያንዳንዱ ድርጅት «ታዲያ እዚህ ውስጥ የኔ ቦታ ምን ይሆናል? ይህ ስትራቴጂ ለድርጅ ቴ ያዋጣል ወይስ አያዋጣም?» ከሚል ወገናዊና አጥፊ ስሌት ከተነሳ ይህ ስትራቴጂ አይሰራም።

በመንደርደሪያ ሰነዱ ላይ ስለኢትዮጵያ ተሃድሶ የተጠቀሙትን አካሄዶች አዋህደን ሁላችንም « ከድርጅቴ አገሬና ህዝቤ ይቅደሙ» ከሚል ራእይ ከተነሳን ግን ይህ አይነቱ አካሄድ ተሞክሮ ቢሳካልን በሃገራችን የሚፈጥረውን፣የፖለቲካ፤ የሞራል፤ የሳይኮሎጂካልና የዲፕሎማቲክ በጎ እምርታ ለመገመት አስቸጋሪ አይመስለንም።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
(ሃምሌ 1995 ዓ.ም.)